# ላንገታችን ገመድ

ከወያኔም በላይ ፣ ከመለስ በከፋ
ጥይት ሳያባክን ፣ ሳይደክም ሳይለፋ
ወሬ በማሳመር ፣ በዲስኩር ልፈፋ
ህልም እያዘገነ ፣ ተምኔታዊ ተስፋ
አይደለም ግለሰብ ፣ አገር አንቀላፋ
ወሬ ላማለለው ፣ ወዶ ለተደፋ
እያስጨበጨበ ፣ መጣ የሚያጠፋ ።

ወሬ በማሳመር ፣ አቻ አይገኝለት
ተግባሩና ቃሉ ፣ አይገጥም ላብነት
አዲሱ መሪያችን ፣ ያጨበጨብንለት
ወደን ባመጣነው ፣ ገባልን ሰንሰለት
አረደን በደነዝ ፣ መች ሆነ በስለት
ከድጡ ወደማጡ ፣ ጋለበን ቁልቁለት ።

እንዲህ ነው እንግዲህ ፣ የሆይሆይታ አባዜ
እያጨበጨብን ፣ ካንዴም ሁለት ጊዜ
ልዩ ፍጡር አርገን ፣ ያልነው ሰው ምርኩዜ
ሆ! ብለን አንግሰን ፣ መልሰን ትካዜ
ለሚሰማው ግራ ፣ አይበጅ ለኑዛዜ ።

አይን ያለው ያስተውል ፣ ጆሮ ያለው ይስማ
ጫጩት አይገኝም ፣ እንቁላል ከገማ
ምድር ላይ ያለውን ፣ ላየና ለሰማ
በአዲስ አበባችን ፣ በሸገር ከተማ
ብርሃን የመሰለህ ፣ ድቅድቅ ነው ጨለማ
ጅቡ ተሸኝቶ ፣ ተጨንቋል በአሳማ ።

ከእባብ እንቁላል ፣ አርግብ ላይወለድ
እንዲያው ያላባቱ ፣ ይሆን ብለን ዘመድ
የተንሸዋረረ ፣ ቅጥ የጠፋው መንገድ
መጥረቢያው ከዛቢያው ፣ መቼም ላይዋደድ
የትዳር ሰማንያው ፣ በጊዜ ይቀደድ
ሸምቀቆ ሳይገባ ፣ ላንገታችን ገመድ ።

ታዛቢው

February 9, 2019